የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ማስታወሻ**

ለ ፡ ኢፌዴሪ ኤምባሲ/ ቋሚ መልዕክተኛ / ቆንስላ ጽ/ቤቶች
፡ ሁሉም ዳይሬክቶሬት ጀኔራሎች፣ ጽ/ቤቶች፣ ማዕከል

ከ ፡ ክቡር ሚኒስትር ዲኤታ ጽ/ቤት
(አህጉራዊ ዘርፍ)

ጉዳዩ፦ ኤርትራ በተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት የተጣሉባትን የማዕቀብ ውሳኔዎች ለማስነሳት የምታደርገውን ጥረት ለማክሸፍና ማዕቀቦቹ በተገቢው ሁኔታ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ከበላይ አመራር የተሰጠውን መመሪያ ይመለከታል።

በአሁኑ ወቅት የኤርትራ መንግሥት በተ.መ.ድ. ፀጥታው ምክር ቤት የተጣለቀባትን የማዕቀብ ውሳኔዎች እንዲነሱ ለማድረግ የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች። ኤርትራ የማዕቀቦቹ ውሳኔዎች ከተጣሉባት ጊዜ አንስቶ በክልላችን ባሉ ሀገራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ፀረ-ሰላም ሽብርተኞችንና ሕገ-ወጥ ድርጅቶችን በተለያዩ መንገዶች በመደገፍ ማዕቀቦቹን እየጣሰች የምትገኝ ከመሆኑም በላይ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በዚህ ድርጊቷ ሳትገታ ማዕቀቦቹ እንዲነሱ ወደ ተለያዩ ሀገሮች በመሄድ የማግባባት ተግባራትን እያከናወነች እንደምትገኝ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ እንቅስቃሴም በቀጣይ እየተጠናከረ እንደሚሄድ ይታመናል።

በዋናው መ/ቤት ያሉ የሥራ ክፍሎችና በውጭ የሚገኙ ሚሲዮኖቻችን በዕቅድ የታገዘ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን በመስራት የኤርትራን ዓላማ ማክሸፍ እንደሚኖርብንና ለዚህም እንዲረዳን የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። ሁሉም ዳይሬክቶሬት ጀኔራሎችና የሚሲዮን መሪዎች የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ዓላማችንን ለማሳካት የተዘጋጀውን የዕቅድ መርሃ-ግብር መሰረት በማድረግ፣ ዲ/ጀኔራሎች በሀገር ውስጥ የሚመለከታቸውን የውጭ ሀገር ኤምባሲዎችንና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም በውጭ የሚገኙ ሚሲዮኖቻችን ደግሞ በሚገኙበት ሀገር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት በመለየት የማዕቀብ ውሳኔዎቹ መነሳት እንደሌለባቸውና በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የማግባባት ስራ እንዲሰሩ ይጠበቃል።

ከላይ ለተገለፀው የዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እንዲረዳ ቀጥሎ የተመለከቱት ዶክመንቶች፡-

1. Concept Note
2. Aide Memorie
3. Action Plan
4. Talking Points
5. የUN Monitoring Group July 2013 ሪፖርት Excerpt፣ ከማዕቀቦቹ ጋር የተያያዙ የተ.መ.ድ.፣የኢጋድና የአፍሪካ ሕብረት ውሳኔዎች

በኢ-ሜይል የተላኩላችሁ ሲሆን፣ ዳይሬክቶሬቶችና ሚሲዮኖች ከዚህ ጋር አባሪ በተደረገው ዕቅድ መነሻ የየራሳቸውን ዝርዝር ዕቅድና መርሃ-ግብር በማውጣት፣ በዕቅዱ መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን ሪፖርት በየሁለት ሣምንት (በወር አጋማሽ እና በወር መጨረሻ) ለክቡር የፖለቲካ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽቤት እና ለሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች፣ ሚሲዮኖች ደግሞ ለሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች፣ በግልባጭ ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ጽቤት እና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዳይሬክቶሬት እንዲላኩ በክቡር ሚ/ር ዴኤታው መመሪያ የተሰጠ መሆኑን እናሳውቃለን።

አባሪ፡- የተጠቀሱት

ግልባጭ፡-

- ለክቡር ሚኒስትር ጽቤት
- ለክቡራን ሚ/ር ዴኤታዎች

## የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያሳለፋቸውን የማዕቀብ ውሣኔዎች አተገባበርና ቀጣይነት አስመልክቶ የምክር ቤቱ አባላትን ለማነጋገር እንዲረዳ የተዘጋጀ መነሻ ጹሑፍ /concept note/

## መግቢያ

የተ.መ.ድ ፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያሳለፋቸው የማዕቀብ ውሣኔዎች በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆኑና ወደፊትም ተጠናክረው እንዲቀጠሉ ለማስቻል፣ የምክር ቤቱን ቋሚና ተለዋጭ አባላት በአዲስ አቀራረብ /new approach/ በመቅረብ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የፀጥታው ምክር ቤት የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ አባል አገራት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ይታወቃል ። እነዚሁ የፀጥታው ምክር ቤት አባላት ደግሞ ውሣኔዎቹን ከመፈፀም ባሻገር ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የማይተካ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

ከዚህ ቀደም ኤርትራ ላይ የተጣሉ ማዕቀቦች እውን ሊሆኑ የቻሉት በዋናነት በኤርትራ በኩል ይወሰድ በነበረው ይፋዊ ጠባአጫሪነት ምክንያት በተፈጠረው የኢጋድ ውስጣዊ አንድነት እንደነበር አይዘነጋም። በሪዞሊሽን 1907 ዝግጅትና ማፅደቅ ሂደት ዩጋንዳ፣ ጅቡቲና ሶማሊያ የተጫወቱት ሚና፣ በሪዞሊሽን 2023 ሂደት ከአገራችን በተጨማሪ ጅቡቲና ኬንያ፣ የነበራቸው ተሳትፎ ጉልህ ነበር።

ከኢጋድ አንድነት ባሻገር በዲሴምበር 2011 ዓ.ም. ተጨማሪ ማዕቀብ ለመጣሉ የሞኒተሪንግ ቡድኑ በየጊዜው ያቀረባቸው ግልጽና በብዙሃኑ ተቀባይነት ያገኙ፣ በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረቱ ሪፖርቶች የተጫወቱት ሚና ቁልፍ እንደነበር አይዘነጋም። ውሳኔ ቁጥር 2023 (2011) ከተላለፈ በኋላም የሞኒተሪንግ ቡድኑ የቁጥጥር ስራውን የቀጠለ ሲሆን፣ በጁላይ 2012 እና ጁላይ 2013 ዝርዝር ሪፖርት ማቅረቡ ይታወሳል።

ጁላይ 2013 ዓ.ም. የወጣው ሪፖርት የኤርትራ መንግስት ለአልሻባብ የሚሰጠው ግልጽ ድጋፍ ቢቀንስም በተዘዋዋሪ መንገድ መቀጠሉን፣ በአካባቢው ላሉ አፍራሽ ሃይሎች የሚሰጠው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንዳለ መሆኑን የሚያብራራ እንደነበር አይዘነጋም። በተጨማሪም ሪፖርቱ የኤርትራ መንግስት የሚጠቀምበትን ዝርዝር የኮንትሮባንድ ዘዴ ማጋለጡ ይታወሳል። ይህም የኤርትራ መንግስት የታክቲካል ለውጥ እንጂ strategic shift አለማድረጉን እንደሚያሳይ በሪፖርቱ ተብራርቷል። ይሁንና ሪፖርቱ ሚዛናዊ አይደለም የሚል ወቀሳ ከራሺያ ፌደሬሽን እንደቀረበበት (በፓኪስታን ሞምር)፣ ሌሎች

በሪፖርቱ ስማችን ያለአግባብ ተጠቅሷል ያሉ አገሮች፦ ማሊያን፣ ኖርዌይ፣ ኬኒያና ሶማሊያ ትሬታ ማስማታቸው ይታወሳል።

በመሆኑም በኤርትራ በኩል ምንም አይነት የፖሊሲና የባህርይ ለውጥ ባልመጣበት ሁኔታ፣ ማዕቀቡን ለማለሳለስ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለማስቆምና ማዕቀቡን በአግባቡ ለመተግበር የተቀናጀ እንቅስቃሴ ማድረጉ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳ ነው።

## 1. በኤርትራ በኩል እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ

በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ወገኖች በኩል የኤርትራ መንግስት ደክሟል፣ የመለሳለስ ሁኔታም እያሳየ ነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራ ከእለም አቀፍ ማህበረሰብ መገለሏ ህዝቡን እየጎዳ ነው ስለዚህ ም/ቤቱም ቢለሳለስ የሚል ሃሳብ እየሰነዘሩ ይገኛል። ለዚህ በቀድሞው የአሜሪካ የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ሚኒስትር ሚ/ር ኸርማን ኮሀን የተፃፈው ፅሁፍ ተጠቃሽ ነው። በተ.መ.ድ. የአፍሪካ ጉዳዮች የሚከታተሉ አካላት በኢኮኖሚና ፖለቲካ ውጥረት ምክንያት ኤርትራ አቋሟን እያለሳለሰች ስለሆነ ከዚሁ ጋር የሚሄድ ምላሽ ያስፈልጋል የሚሉ አስተያየቶች መሰማት ጀምረዋል። በCongress አካባቢና እንደ US Council of Foreign Relations (CFR) በመሳሰሉ ተቋሞች አካባቢ ይህንኑ የመሰለ ሃሳብ በመንሸራሸር ላይ እንደሆነ ምልክቶች አሉ።

እስከአሁን ለማዕቀቡ በጥናንት ድጋፍ ይሰጡን የነበሩት የአፍሪካ አገሮች (ቀደም ሲል ፔጋንዳ 1907፣ ጋቦን ደግሞ 2023 እንዲፀድቅ፣ በትርቡ ደግሞ አፈጻጸምን በተመለከተ ያለውን ወቅታዊ መረጃ በመስጠት ሞርኮ) እንደነበሩ አይዘነጋም። ሌላው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ኤርትራን በተመለከተ ኢጋድ ውስጥ የነበረው አንድነት -ኤርትራ በምታሳየው deceptive charm offensive ምክንያት (በኬንያና በሱዳን የተደረጉት ጉብኝቶች፣ በናይሮቢ ተይታቸው ከፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር እና ከታንዛኒያና DRC ፕሬዝዳንቶች ጋር መነጋገራቸው) እንዳይጎዳ ስጋት መኖሩ ነው።

በኤርትራ በኩል፣ አሁን ካለበት isolation ለመውጣት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ነው። ፕሬዝዳንት ኢሳያስ በትርቡ በኬንያና በሱዳን ያደረጉት ጉብኝት፣ የተለያዩ የተ.መ.ድ. አካላት (UNDP, OCHA) ኃላፊዎች አስመራን እንዲጎበኙ በማድረግ ኤርትራ ተለውጣለች የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ የሚደረገው እንቅስቃሴ፣ አቶ የማነ ገብረ ዓብ በፓሪስ ያደረጉት ጉብኝት ተጠቃሽ ናቸው። የኤርትራ ባለስልጣናት ከሞኒተሪንግ ቡድኑና ከማዕቀብ ኮሚቴው ሊተመገበር (ከኮርያ አምባሳደር)

ጋር ዲሴምበር 6/7 በፓሪስ ያደረጉት ውይይት የዚሁ አካል ይመስላል። ይህ እንቅስቃሴ ከአለም አቀፍ ህብረተሰብ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ያለመ ቢሆንም ዋናው ግብ የማዕቀቡ ጉዳይ እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። በተ.መ.ድ. በኩልም ከዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ በኤርትራ በኩል የመተባበር ፍላጎት (በፖለቲካ ጉዳዮች ጭምር) እንደታየ ይገልጻሉ።

ባጠቃላይም፣ ማዕቀብን አስመልክቶ ያለው አሉታዊ አመለካከት፣ በተለይም በመልማት ላይ ባሉ አገሮች አካባቢ፣ ለኤርትራ ምቹ ሁኔታን ሳይፈጥር እንዳልቀረ መገመት ይቻላል። በቅርቡ በጀኔቫ በተደረገው የኤርትራ UPR አገሪቱ ያገኘችው ድጋፍ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። በወቅቱ እንደ ዩጋንዳ ያሉ ኤርትራን በመደገፍ የተናገሩት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ

## 2. ኢጋድን በተመለከተ

ከላይ እንደተጠቀሰው ለኤርትራ ማዕቀብ መጣልና መጠናከር (ከአፍሪካ ሕብረት እስከ ፀጥታው ም/ቤት በነበረው ሂደት) በኢጋድ ውስጥ የነበረው አንድነት ወሳኝ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ተሸርሽር ጉዳዩ የኢትዮጵያና ኤርትራ ተደርጎ ከተወሰደ አገሮች የኤርትራ narrative ወደሆነው " የችግሩ ሁሉ ምንጭ የድንበር ችግሩ ነው" ወደሚል እንዲሄዱ ሊያደርግ የሚችልበት እድል ሰፊ ነው። ስለዚህ የኢጋድን አንድነት ማጠናከር ለዚህም በተለይ ከጅቡቲና ከኬንያ ጋር በቅርበት መስራት አማራጭ የለውም።

በኢጋድ ውስጥ ያለውን አንድነት ማጠናከር ለዚህም በክልሉ የፀጥታና የደህንነት አካላት በኤርትራ በኩል እየተደረገ ያለው አፍራሽ እንቅስቃሴ በሚመለከት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በጉዳዩ ላይ የተሻለ መግባባት እንዲፈጠር ከሚመለከታቸው የአገራችን መ/ቤቶች ጋር መንቀሳቀስ መልካም ይሆናል።

## 3.የሞኒተሪንግ ቡድኑን በተመለከተ

ከላይ እንደተቀመጠው በሞኒተሪንግ ቡድኑ ሲቀርቡ የበነሩ ሪፖርቶች በኤርትራ ላይ የተጣሉ ማዕቀብ እንዲጠናከርና ተጠብቆ እንዲቀይ ቁልፍ ሚና ነበራቸው። ይሁንና የሞኒተሪንግ ቡድኑ የጁላይ 2013 ሪፖርቱን ሲያቀርብ ከተለያዩ ወገኖች (በተለይ ከኤርትራ በኩል) ጠንካራ ተቃውሞና የማጥላላት ዘመቻ ደርሶበታል። ቡድኑ በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው ሪፖርቶች የሶማሊያ መንግስት በሙስና መዘፈቁንና የኬንያ ሠራዊት አባላት በኪስማዮ የከሰል ንግድ በሰፊው እንደተሰማሩ መግለጹ ይታወሳል። የሶማሊያ መንግስት የቡድኑ መሪ እንዲነሱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለዋና ፀሐፊው ልኳል። ተመሳሳይ ተቃውሞና ደብዳቤና የpersona-non-grata ማስፈራሪያ በኬንያም በኩል ተሰንዝሮ እንደነበር አይዘነጋም። ከዚህ

ጋር በተያያዘም አንድ በዜግነት እንግሊዛዊ (በትውልድ ናይጀርያዊ የሆኑ የቡድኑ አባል ወደናይሮቢ እንዳይገቡ የተከለከሉ ሲሆን፤ የኬንያ መንግስት በተ.መ.ድ. የተረበሰትን ተደጋጋሚ የቪዛ ጥያቄ ሳይቀበል ቀርቷል።

ይህ ሁኔታ በኤርትራ በኩል ቡድኑ neutral አይደለም በሚል ከሚመጣው ግፊት ጋር ተደምሮ የቡድኑን ተዓማኒነት እንዳይጎዳው ስጋት አለ። ማዕቀቡ በም/ቤቱ ውስጥ የሚኖረው ድጋፍ (በተለይ ቋሚ ባልሆኑ አባላት በኩል) በዚህ ቡድን ሪፖርት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤ የቡድኑ ተዓማኒነት መጎዳት ማዕቀቡ ያለውን ድጋፍ እንዳይጎዳው ያሰጋል።

እንደሚታወቀው የሞኒተሪንግ ቡድኑ integrity እና የሚያቀርባቸው ሪፖርቶች ተዓማኒነት ለማዕቀቡ የጀርባ አጥንት ነው። በአሁኑ ወቅት በቡድኑ ላይ ከተለያዩ ወገኖች (ሶማሊያና ኬንያን ጨምሮ) የሚሰነዘረው ወቀሳ፤ ኤርትራ ቡድኑ የአሜሪካና የኢትዮጵያ መሣሪያ ነው በሚል ከምታካሂደው ዘመቻ ጋር ተደምሮ ተዓማኒነቱን እንዳይጎዳው ስጋት አለ። የሞኒተሪንግ ቡድኑ credibility እንዳይጎዳ ከቡድኑ ጋር ተቀራርቦ መስራት፤ ቡድኑ ከሶማሊያ እና ከኬንያ መንግስታት ጋር ያለውን አለመግባባት እንዲፈታ የማግባባት ስራ መስራት፤ ተገቢ ይሆናል። በኢጋድ ውስጥ የምንፈጥረው መቀራረብና የጋራ አመለካከት ለሞኒተሪንግ ቡድኑ የሚሰጠውን ድጋፍም ሊያጠናክር ይችላል።

## 3. የም/ቤቱን አባላት በተመለከተ

### I. አምስቱ ቋሚ አባላትን በተመለከተ

**አሜሪካ**

አሜሪካ በኤርትራ ላይ የተጣሉት የማዕቀብ ውሳኔዎች (1907/2009) እና 2023/2011) በተከታታይ እንዲተላለፉ ጠንካራ እንቅስቃሴ አድርጋለች። በዚህ ረገድ በወቅቱ የነበሩት በተ.መ.ድ የአሜሪካ ቋሚ መልእክተኛ Ambassador Susan Rice ውሳኔዎቹ እንዲተላለፉ እንዲሁም የኤርትራን ባህሪ ጠንቅቆ በማወቅና የሻቢያ መንግሥት በአካባቢያችን የሚያደርጋቸውን እኩይ ተግባራት በማጋለጥ ረገድ ያደረጉት አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል።

አሜሪካ ኤርትራን በተመለከተ በተ.መ.ድ ዋና ፀሐፊና በሞኒተሪንግ ቡድኑ ሪፖርቶች በሚተርቡበት ወቅት አገሪቱ በሶማሊያና በአካባቢያችን የምታራምደውን አፍራሽ ተግባራት በማውገዝና አገሪቱ ከዚሁ ድርጊቷ እንድትታቀብ በተደጋጋሚ አሳስባለች። ከዚህ በተጨማሪ ኤርትራ ከመለሳለስና በታክቲካል ደረጃ ከመለወጥ ባለፈ እውነተኛ /genuine/ እና ተጨባጭ ለውጥ እንዳላመጣች በአሜሪካ መንግስት በኩል እንደሚታወቅ አዲስ አበባ ከሚገኘው የአገሪቱ ኢምባሲ ዲፕሎማት በተደጋጋሚ ለመረዳት ችለናል።

በአሁኑ ወቅት በተ.መ.ድ የአሜሪካ ቋሚ መልክተኛ የሆኑት Ambassador Samantha Power በኤርትራ ላይ እንደ Ambassador Susan Rice ጠንካራ አቋም ላይኖራቸው ይችላል ብሎ መገመት ቢቻልም እንደ አሜሪካ መንግስት ተወካይ አገሪቱን በተመለከተ የተለየ ወይንም የተለሳለሰ አቋም ያራምዳሉ ለማለት አይቻልም። በዚህ ረገድ በአወንታዊ ጉን የሚታየው Ambassador Susan Rice የፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ስለሆኑ፤ አሜሪካ እንደ አገር በኤርትራ ላይ የምትከተለው ፖሊሲ በተጣይ ጊዜያት ይለወጣል ብሎ ማሰብ ያዳግታል።

ሆኖም ግን ኤርትራ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጀመረችው የዓለም አቀፍ ማህበረሰብን engage የማድረግ አካሄድ ተጠናክሮ ከቀጠለና የአንዳንድ አገሮችን (ቻይና እና ራሺያ) ቀልብ ከሳበች፤ የፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባላትን የመከፋፈል እድል ልታገኝ ትችላለች። በመሆኑም አሜሪካ በያዘችው አቋም እንድትቀጥልና ውሳኔዎቹን ተፈፃሚ እንድታደርግ ለማስቻል ኤርትራ ተጨባጭ የባህሪ ለውጥ እንዳላመጣች እስረግጦ ማስረዳትና ከMine Sector የምታገኘው ገቢን ለመቆጣጠር እንዲቻል መዘጋጀት ያለበት Due Diligence Guidelines ተጠናቆ ተግባራዊ እንዲሆን ማሳመን ያስፈልጋል።

**እንግሊዝ**

የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያሳለፋቸውን ሁለት የማዕቀብ ውሳኔዎች እንግሊዚ መደገፏና አገሪቱን በተመለከተ በአጠቃላይ የምታራምደው አቋም ከአሜሪካ ጋር ተመሣሣይ እንደሆነ የታየ ጉዳይ ነው። እንግሊዝ የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ የጣለውን የጦር መሣሪያ ማዕቀብ (1907/2009) ተከትላ The Export Control Order 2011 (S1 2011/1296) የሚባል ሕግ ያወጣች ሲሆን፤ በሕጉም የአውሮፓ ሕብረት በዚሁ የምክር ቤቱ ውሳኔ በኤርትራ ላይ የጣለውን የጦር መሣሪያ ማዕቀብ በእንግሊዝ በኩል በአግባቡ ተፈፃሚ ለማድረግ እንዲቻል ነው።

በመሆኑም እንግሊዝ የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ለጣላችው ማዕቀቦች እና ለሞኒተሪንግ ቡድኑ የምትሰጠው ድጋፍ በአጭር ጊዜ ይቀየራል ብሎ ለመገመት እንደማይቻል በኒውዮርክ ከእንግሊዝ ቋሚ መልዕክተኛ ጋር የተደረገው ውይይት ይጠቁማል። በተጨማሪም ማዕቀቦቹ ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በአግባቡ

እንዲፈፀሙ እንዲሁም ብዙ ጊዜ የወሰደው የDue Diligences Guidelines ዝግጅት ተጠናቆ ስራ ላይ እንዲውልና ኤርትራ እውነተኛ የባህሪ ለውጥ እንዳላመጣች በማስረዳት ከእንግሊዝን ጋር ተቀራርቦ መስራት መቀጠል አግባብ ይሆናል።

**ፈረንሣይ**

ፈረንሣይ የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያሳለፋቸው ሁለት የማዕቀብ ውሣኔዎች ሲፀድቁ ሙሉ ድጋፍ መስጠቷ ይታወሳል። ለዚህ የፈረንሣይ አቋም ዋናው ምክንያት ኤርትራ በቀጠናው የምታደርገው ፀረ-ሰላም እንቅስቃሴና ለአሸባሪ ሐይሎች የምትሰጠው ድጋፍ ቢሆንም፣ አገሪቱ በ2008 የጅቡቲን ድንበር በመጣስ ወረራ ማካሄዷና እስካሁን ድረስ ምርኮኛ ወታደሮችን አለመመለሷ በሁለት አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት በጥሩ ደረጃ ላይ እንዳይሆን አድርጉታል።

በፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባላት መካከል ባለው አሰላለፉ መሠረት በተለያዩ የአለም አቀፍ ሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች (ኤርትራን ጨምሮ) አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ በአብዛኛው ተመሣሣይ አቋም እንደሚያራምዱ ይታወቃል። እስካሁን ባለው ሁኔታም ፈረንሣይ በኤርትራ ላይ ለተጣሉት ማዕቀቦች እና ለሞኒተሪንግ ቡድኑ ድጋፍ እየሰጠች ሲሆን፣ ይኸው እንደሚቀጥል በቅርቡ ከፈረንሳይ የተ.መ.ድ. ቋሚ መልእክተኛ ጋር የተደረገው ውይይት ያረጋግጣል። በቀጣይ የDue Diligence Guidelines ዝግጅቱ ተጠናቆ ተግባር ላይ እንዲውል የፈረንሳይን ድጋፍ ለማግኘት መንቀሳቀስ ተገቢ ይሆናል።

**ራሺያ ፌደሬሽን**

ራሺያ የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ 1907/2009 ውሳኔን ሲያስተላልፉ የደገፈች ቢሆንም፣ ሁለተኛው ውሳኔ 2023/2011 ላይ ግን ድምፅ ተአቅቦ አድርጋለች። ይህ ብቻ ሳይሆን ራሺያ ከደቡብ አፍሪካ እና ከቻይና ጋር በመሆን ውሣኔው ጠንካራ እንዳይሆን ይዘቱን water down አድርጋለች። ለዚህም የአቋም ለውጥ እንደምክንያት የሚቀጠረው ከኢትዮጵያ ጋር ያለው የግንኙነት ሁኔታ ሳይሆን፣ የምክር ቤቱ አባላት ሌሎች አገሮችን (አይቮሪኮስትና ሊቢያ) አስመልክቶ የአቋም ልዩነት መያዛቸው ነው።

አገራችን ከራሺያ (አስቀድሞም ከሶቭየት ሕብረት) ጋር ካላት ዘመናትን ካስቆጠረ ግንኙነት አንፃር፣ ምክር ቤቱ በኤርትራ ላይ የጣላችው ማዕቀቦች እንዲነሱ ድጋፏን እንደማትሰጥ ይገመታል። ሆኖም ግን አሁን በምክር ቤቱ አባላት መካከል ባለው ፉክክርና የበላይነት ለመያዝ በሚደረገው እንቅስቃሴ በP3 (አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ) በኩል በኤርትራ ላይ ጠንካራ አቋም ከተያዘና አገሪቱ ማዕቀቦቹ እንዲነሱ ለማድረግ አሁን በጀመረችው አኳኋን ቀጥላ የራሺያን አወንታዊ ምላሽ ካገኘች፣ አገራችን በኤርትራ ላይ የተጣሉት

ማዕቀቦች በአግባብ እንዲተገበሩና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ያሰበችው ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ፈተና ሊገጥመው ይችላል።

ሆኖም ግን በቅርቡ የኒውዮርክ ሚሲዮናችን እዛው የሚገኙትን የራሺያን አምባሳደር አግኝቶ ባናገራቸው ወቅት አምባሳደሩ አገራቸው ኢትዮጵያን ለመደገፍ ዝግጁ እንደሆነች፣ ኢትዮጵያን ከኤርትራ ጋር እንደማያወዳድሩና በራሺያ በኩል ኢትዮጵያን objective ከሆነውም በላይ በመሄድ ለማገዝ ዝግጁነት እንዳለ ገልፀዋል። በመሆኑም በዚህ ላይ build በማድረግ ኤርትራ እውነተኛ የባህሪ ለውጥ እንዳለመጣች በሚገባ በማስረዳት፣ ምክር ቤቱ በኤርትራ ላይ የጣላቸው የማዕቀብ ውሣኔዎች በአግባቡ መተግበርና ሳይነሱ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው እንዲሁም ሂደቱ የተንተተው Due Diligence Guidelines ተጠናቆ በስራ ላይ እንዲውል ራሺያ ድጋፍ እንድታደርግ በሚገባ ማሳሰቡ ተገቢ ነው።

<u>**ቻይና**</u>

ቻይና በመርህ ደረጃ ምንም ዓይነት ማዕቀብ በአገሮች ላይ መጣል የለበትም የሚል አቋም እንደምታራምድ ይታወቃል። ይህ አይነቱ የቻይና ከተ.መ.ድ ቻርተር ጋር የማይጣጣምና ከአንድ የፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል የማይጠበቅ አቋም ለኤርትራ ጠቅሟታል። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው ቻይና በኤርትራ ላይ የተላለፉት ሁለት የማዕቀብ ውሣኔዎች (1907/2009 እና 2023/2011) ሲተላለፉ ድምፅ ተአቅቦ ማድረጓና ከራሺያ ጋር በመሆኑ ሁለተኛው ውሣኔ water down እንዲሆን ጠንካራ አቋም መያዟ ነው።

ይህ የቻይና አቋም የሚታየው ከprinciple አንፃር ብቻ መሆን የለበትም። እንደሚታወቀው ቻይና ከኤርትራ ጋር የኢኮኖሚና ሎሎች ግንኙነቶች ያላት ሲሆን፣ በዚህ ምክንያት ቻይና ኤርትራን ማስቀየም አትፈልግም። በሌላ በኩል በፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባላት መካከል ያለው ክፍፍልና የበላይ ለመሆን የሚደረገው ጥረት እንደ ኤርትራ ያሉ ሕገ-ወጥ አገሮችን ጠቅሟል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ አገሪቱ የኤርትራን የፖለቲካና ወታደራዊ መሪዎች ዝውውር ለማገድና በአገሪቱ ኢንቨስት የሚያደርጉ ኩባንያዎችን አስመልክቶ የፋይናንስ ቁጥጥርና ክትትል ይደረግ የሚለውን ሐሳብ ቻይና በተደጋጋሚ መቃወሟ ነው። ምንም እንኳን ቻይና ይህ አካሄድ የሚጐዳው ሕዝቡን ነው የሚል ምክንያት ብትሰጥም፣ ጉዳዮን ከዚህ ባለፈ ማየቱ ተገቢና ጠቃሚ ነው።

በመሆኑም ኤርትራ ማዕቀቦቹ እንዲነሱ የጀመረችው ጥረት በቻይና በኩል ተቀባይነት እንዳያገኝ፣ አገራችን የኤርትራን አለመለወጥ እንዲሁም የማዕቀቡ ጉዳይ የኢትዮጵያና ኤርትራ ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ ማስረዳትና የኤርትራ የማተራመስ ፖሊሲ ከድንበር ጉዳይ ጋር ፈጽሞ እንደማይገናኝ አስረግጠ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

## II. በ2014 የፀጥታው ምክር ቤት አባል የሆኑ አገራትን በተመለከተ

### ናይጀሪያ

ናይጀሪያ የኤርትራ መንግስት የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን ለማተራመስ በሚከተለው ፖሊሲ የተነሣ፣ የፀጥታው ምክር ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ያሳለፈውን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ውሣኔ (2023/2011) ከጋቦን ጋር co-sponsor በማድረግ በምክር ቤቱ አባልነቷ ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች። እንደሚታወሰው የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ማዕቀቦችን ሲጥል ከአፍሪካ አገሮች ሊቢያ የመጀመሪያውን ውሣኔ የተቃወመች ሲሆን፣ ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ሁለተኛ ውሣኔ ሲተላለፍ ምንም እንኳን በመጨረሻ ላይ ብትደግፍም አስቸጋሪ ነበረች፡፡

አገራችን ከናይጀሪያ ጋር በአፍሪካ ሕብረትና በተለያዩ መድረኮች ተቀራርባ በመስራት ላይ ትገኛለች። አገሪቱ ምንም እንኳን በዋናነት በምዕራብ አፍሪካ ሪጅናል ሚካኒዝም (ECOMOG) በኩል በተለይም በቀጠናው ሰላም ፀጥታን በማስከበር ረገድ ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ላይ ስትሆን፣ በዳርፉር የሰላም አስከባሪ እንዲሁም በሶማሊያ አነስተኛ ቁጥር ያለው የፖሊስ ሐይል አስማርታለች።

አገራችን በቀጣይ በኤርትራ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች ለአባል አገራት በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆኑና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለምታደርገው ጥረት፣ ናይጀሪያ በተሻለ ሁኔታ ትብብር እንደምታደርግና አቋማችንን እንደምትደግፍ የሚጠበቅ ሲሆን፣ ከአገሪቱ ጋር በተለይም በኒውዮርክ ሚሲዮናችን በኩል በይበልጥ ተቀራርቦ መስራቱ አስፈላጊ ነው።

### ቻድ

ቻድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማሊና በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ ነች። እየተጫወተች ባለችው ጉልህ ሚና የተነሣ መታወቅ ጀምራለች። አገሪቱ ለፀጥታው ምክር ቤት አባልነት ከተመረጠች በኋላ፣ የኒውዮርክ ሚሲዮን በሰው ሐይል የማጠናከርና ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ያገለገሉ አምባሳደሯን የመመደብ ተግባራትን ስላከናወነች ከናይጀሪያና ሩዋንዳ ጋር በመሆኑ በምክር ቤቱ የተሻለ እንቅስቃሴ እንደምታደርግ ይጠበቃል።

ቻድ ለማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ Seleka አማጽያን ወታደራዊ ድጋፍ እንደምትሰጥ በአለም አቀፍ ሚዲያዎች በብዛት የተዘገበ ሲሆን፣ አማጽያኑ በኤፕሪል 2013 በንጃሜና ቤተ-መንግስት ላካሄዱት የመጨረሻ የጥቃት ውጊያ ከኤርትራ የተገዙ የጦር መሣሪያዎች እንደተጠቀሙም ተገልጿል። የኤርትራው ፕሬዝዳንትም አስቀድሞ ማለትም በጃንዋሪ 12/2011 በተከበረው የቻድ የነፃነት በዓል ላይ ተካፍለዋል።

ሆኖም ግን ከዚህ በመነሣት ቻድ የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ የጣለባት ማዕቀቦች እንዲነሱ አገሪቱ ለጀመረችው ጥረት ሙሉ ድጋፍ ትሰጣለች ማለት አስቸጋሪ ነው። በአገራችን በኩል የኢጋድና የአፍሪካ ሕብረት ሪኮመንዴሽኖችን መሠረት በማድረግ ለቻድ የኤርትራን ተጨባጭ ባህሪ የመግለፅ እንዲሁም ማዕቀቦቹ በአግባቡ እንዲፈፀሙና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የማስገንዘብ ስራ መስራት ይኖርብናል። በፀጥታው ም/ቤት የአንድ አፍሪካን አገር ድጋፍ ማግኘት ለኤርትራ ከፍተኛ ትሩፋት ሲሆን፣ ለማዕቀብ ሂደቱ ከፍተኛ ጉዳት ነው። በመሆኑም በዋናው መ/ቤትም በኒውዮርክ ሚሽን በኩል ቻድ ላይ ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስ አግባብ ይሆናል።

**ሉትዌንያ**

ሉትዌንያ የፀጥታው ምክር ቤት አባል ስትሆን ይህ የመጀመሪያዋ ነው። ሉትዌንያ ከአሜሪካ ጋር መልካም ግንኙነት ያላት ሲሆን፣ በአውሮፓ ሕብረት አባልነቷም የሕብረቱን አቋሞች ስታራምድ ይታያል። ይህ የውጭ ፖሊስዎ ኤርትራ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆኑና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለምናደርገው እንቅስቃሴ ሊረዳ እንደሚችል ይገመታል።

ኖቬምበር 26 ቀን 2013 የሉትዌንያ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከክብር አምባሳደር ብርሃነ ገ/ክርስቶስ ጋር በአዲስ አበባ ተገናኝተው ባደረጉት ውይይት ሉትዌንያ ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማሲያዊ ግኙነቷን ለማጠናከር ጽኑ ፍላጉት እንዳላት ገልፀዋል። በዚህ ረገድ አገሪቷ በኤርትራ የተጣሉት ማዕቀቦች እንዲተገበሩና ተጠናክረው እንዲቀጠሉ ለምናደርገው ጥረት በጣም ጠንካራ ደጋፊ ባትሆንም፣ የአገራችንን አቋም የሚጐዳ ድርጊት ትፈፀማለች ለማለት ያዳግታል። ስለሆነም በቀጣይ አገራችን ሉትዌንያን በመቅረብና የኤርትራን እውነተኛ ባህሪ በማስረዳት፣ ማዕቀቦቹ በአግባቡ እንዲተገበሩና ወደፊትም ተጠናክረው እንዲቀጠሉ ጉዳዩን በአግባቡ ማስጨበጥ ያስፈልጋል።

**ቺሊ**

ባለፉት ዓመታት በታየው trend፣ ከላቲን አሜሪካ የምክር ቤቱ አባል የነበሩ አገራት በአብዛኞዎቹ ከምዕራብ አገሮች ጋር ተፃራሪ የሚባል አቋም ሲያራምዱ ተስተውሏል። በሌላ በኩል በቅርቡ ከሪጅኑ ምክር ቤቱን የተቀላቀሉ አገሮች (ጓቲማላ፣ ኮሎምቢያ እና አርጀንቲና) አፍሪካን በተመለከተ በንቃት ተሣትፎ ሲያደርጉ አልታየም። የላቲን አሜሪካ አገሮች በምክር ቤት ቆይታቸው አብዛኛው ትኩረታቸው በሚወክሉት ሪጅን ጉዳዮች ላይ እንደነበረ ለመረዳት ተችሏል።

ቺሊ ከአስር ዓምት በፊት (2002- 2004) የምክር ቤቱ አባል ነበረች። በወቅቱ በምክር ቤቱ ጉዳዮች ላይ /በተለይም አፍሪካን በተመለከተ/ ትርጉም ያለው ተሣትፎ አድርጋለች ለማለት አይቻልም። ሆኖም ግን አገሪቱ በምክር ቤቱ ቆይታዋ የኢትዮጵያና ኤርትራ ጉዳይ በአጀንዳ ተይዞ ውይይት በሚደረግበት ወቅት፣ ሁኔታው ከአለም አቀፍ ሕግ አንፃር ሲታይ ኤርትራ የተሻለ cause እንዳላት የገለፀችበት ጊዜ ነበር። በሌላ በኩል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቺሊ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀራረብ ፍላጐት ያሳየች ሲሆን፣ ለዚህም አገራችን የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫ ስለሆነችና ቺሊም የላቲን አሜሪካ አገሮች ድርጅት ጽ/ቤት በዋና ከተማዋ ስለሚገኝ ይህ መመሳሰል በሁለት አገሮች መካከል የተሻለ ግንኙነት እንዲኖር ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል።

ቺሊ በፀጥታው ምክር ቤት በአሁኑ አባልነቷ ለኤርትራ ወግና የኢትዩጵያን ጥቅም የሚጐዳ አቋም ታራምዳለች ብሎ ሙሉ በሙሉ መገመት አይቻልም በቅርቡ በኒውዮርክ ከቺሊ ቋሚ መልእክተኛ ጋር በተደረገው ውይይት ይህንኑ ማረጋገጥ ተችሏል። በአገራችን በኩል የቅርብ engagement ፈጥሮ አቋማችንን እንድትረዳ ማድረግና በኤርትራ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች በአግባቡ መተግበርና ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

## ጆርዳን

ጆርዳን የምክር ቤቱ ተለዋጭ አባል የሆነችው ሳውዲ አረቢያ በአባልነት ከተመረጠች በኋላ withdrew በማድርጓ ነው። ጆርዳን ከኤርትራ ጋር ያላት ግንኙነትን ለማጠናከር በማሰብ ኖቬምበር 30/2013 የየመን አምባሳደሯን Mr. Suleiman Ghweiri በኤርትራ Non Resident Ambassador አድርጋ ሾማለች። የሁለቱ አገሮች ትብብር የሚጠናከሩበት ዘርፎችም ጤናና ትምህርት እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል።

ጆርዳን የጃንዋሪ 2014 የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ነች። በወሩም ውስጥ በመካከለኛ ምስራቅ፣ በሶሪያና የመን ላይ open sessions አዘጋጅታ በሊቀ- መንበርነት መርታለች። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጆርዳን ትኩረት የምትሰጣቸው አለም አቀፍ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ሲሆን፣ ኤርትራን በተመለከተ non-resident ambassador መሰየሟ ከአገሪቱ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር እንደወሰነች ያስረዳል።

በመሆኑም በአገራችን በኩል ጆርዳንን በመቅረብ ኤርትራ በቀጠናችን የምታደርገውን የማተራመስ እንቅስቃሴን እንዳለቆመች በማስረዳት፣ በምክር ቤቱ የተጣሉት የማዕቀብ ውሣኔዎች በአግባቡ ተፈፃሚ መደረግና በተጨማሪም ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ማስረዳት ያስፈልጋል።

## III. በምክር ቤቱ ለአንድ ዓመት በአባልነት የቆዩ አገሮችን በተመለከተ

ሩዋንዳ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ አርጀንቲና፣ ሉክሰምበርግና አውስትራሊያ በምክር ቤቱ ተለዋጭ አባልነት ለተጨማሪ አንድ ዓመት (2014) ይቆያሉ። የኒውዩርክ ሚሲዮናችን አገራቱን አስመልክቶ በቅርቡ በሰጠው አስተያየት ደቡብ ኮርያና አውስትራሊያ በአብዛኛው ከአሜሪካ ጋር የሚመሳሰል አቋም እንደሚያራምዱና በአንፃሩ አርጀንቲናና ሉክሰምበርግ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ወይንም ተሣትፎ እንደማያደርጉ ገልጿል። ሩዋንዳም ከሚሲዮናችን ጋር በተለያየ ደረጃ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ምክክሮችን ብታደርግም፣ ኤርትራን በተመለከተ forthcoming በመሆን ጠቃሚ መረጃዎችን መስጠት እንዳልቻለች ተገልፃል። በመሆኑም አገሮቹን አስመልክቶ የኒውዩርክ ሚሲዮናችን firsthand መረጃ ስላለው፣ በቀጣይ በኤርትራ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች በአግባቡ እንዲተገበሩና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በምናደርገው ጥረት ከሚሲዮኑ ጋር እየተመካከሩ መንቀሳቀሱ ተገቢ ይሆናል።

### 4. ማጠቃለያ

በኤርትራ ላይ የተጣለው ማዕቀብ ችግር ውስጥ ገብቷል ባይባልም፣ ፈተና ላይ እንደሆነ ብዙ ምልክቶች አሉ። በአርግጥ ማዕቀቡን ለማንሳት በቀላሉ የሚቻል አይደለም። ዞሮ ዞሮ እርሳሱን (pen) የያዘችው አገር፣ ዩናይትድ ስቴትስ አቋሟን እስካልለወጠች ድረስ የማዕቀቡ መነሳት አደጋ አይኖርም። ሆኖም፣ የበለጠ ጥርስ የሌለው እንዲሆንና ቀስ በቀስም እየተቦረቦረ የሚሄድበት ዕድል ዝግ አይደለም። ይህንን ለመከላከል ነው በኛ በኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚገባን። የዚህ ማስታወሻ አላማም ይኼው ነው። በመሬት ላይ በኤርትራ በኩል የሚደረገው አደገኛ እንቅስቃሴ ሳይለወጥ፣ በብልጣብልጥነት ብቻ ኤርትራ ማዕቀቡ ጥርስ እንዳይኖረው የምታረገው አደገኛ እንቅስቃሴ ከተሳካላት መዘዙ ከባድ ሊሆን ይችላል። በመጠኑም ቢሆን ማዕቀቡ ኤርትራን Marginalize ለማድረግ መርዳቱ ብዙም የሚያጠያይቅ አይደለም። በመሆኑም ነው በኤርትራ በኩል ከፍተኛ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ያለው። የኛ Challenge በኤርትራ ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ሳይሆን የIGAD መሆኑን ማስረገጥ ላይ ነው። ይህ ቅድሚያ የሚሰጠው ግብ ሆኖ ርብርብ ሊደረግለት ይገባል።